## ትንሽዋ ታዝማኒያዊት

# የካቲ የአትክልት ቦታ



በShiloh Longbottom
የተገለፀ

Amharic | አማርኛ



በአንድ ወቅት ፋብሪካ ነበር።
ከዚያም ጠፋ።
አሁን ልጆች እንኳን
የማይጫወቱበት ባዶ ቦታ ሆነ።



ካቲ ታዝማኒያዊት ነች፣
በዚህ አቅራቢያ የምትኖር ልጃገረድ ነች።
በዚህ በተረሳ ስፍራ ትራመዳለች፣ እናም
ቆም እያለች ለምን ብላ ትገረማለች።




ካቲ አንድ የምታውቀው ሰው ድስት
ተሸክሞ አየች።
አንድ ወይም ሁለት ተክል ቦታዋን
ሊያሻሽል ይችል እንደሆነ ታስባለች።

John (ጆን) ቀላል አይሆንም፣ ነገር ግን አንዳንድ ዛፎችን መትከል ይቻላል ብሎ ተናገረ።
"ለምን ጥቂት አበቦችን አናበቅልም እናም ለንቦች መኖሪያ አናበጅም?"






ነገሮችን አንድ ላይ በማድረግ ነው
እዚህ ነገሮችን የምናከናውነው።
ጎረቤቶቻችን እኛን ለመርዳት ተሳተፉ።
ከሩቅ እና ከቅርብ ነው የሚመጡት።

በክረምት እንዘጋጃለን።
ቀዝቃዛ ቢሆንም ሁሉም ወደ ህይወት የሚመጣበት ጊዜ ነው።
Mars (ማርስ) የዘር ከረጢቶች ይዛ እዚህ አለች።
ሌሎች ጓደኞች መጡ።






ሥራው ከባድ ነው። ህልማችን ትልቅ ነው።
እንተክላለን፣ ቈፍረን ደግሞ እንዘራለን።
የአትክልት ቦታችን እንዲያድግ ለመርዳት አዳዲስ
ነገሮችን መማር እና መሞከር ያስደስታል።



David (ዴቪድ) መሳሪያ ዕቃዎቹን ይዞ መጣ።
የአትክልት ቦታን እንገነባለን።
ዝናብ ይዘንባል ከዚያም ፀሐይ ወጣች።
የአበባውን መደብ እንንከባከባለን።




ሌዘርዉድ እና ቀጤማ (የቅርጫት ሳር)
ሁል ጊዜ እዚህ ይበቅላሉ።
ማተን በርድስ የሚባሉ አእዋፍ እና
ዎምባቶች ብቅ ማለት ጀምረዋል።



በበጋ ውሃ ያስፈልገናል።
Carleeta (ካርሊታ) መንገዱን ታውቀዋለች።
ሁሉ ጊዜም እንደዚህ ነው።
ለዚህ ነው እዚህ የምንኖረው።

Katy (ካቲ) ታዝማኒያዊት ነች። ባዶ የነበረ ቦታ ወስዳ የአትክልት ቦታ ለማሰናዳት ከጓደኞቿ ጋር ትሰራለች።





ሁላችንም ትልቅም ሆነ ትንሽ የራሳችን
ተሰጥኦ አለን።
ካቲ አደረገችው! እርስዎም ማድረግ ይችላሉ...

አስተውል!
በሁላችንም ውስጥ ትንሽ ታዝማኒያዊት አለች።



አዎ፣ ያቺ አንቺ ነሽ።

# እነዚህን የታዝማኒያ እንስሳት መለየት ይችላሉን?

1

ፕላቲፐስ

2

የታዝማኒያ እንቁራሪቶች
(Tasmanian froglets)

3

ረጅም ጆሮ ያላቸው የታዝማኒያ የሌሊት ወፎች

4

ኢምፐረር ጋም የእሳት እራት

5

የተለመዱ ወምባቶች

6

ታዝማኒያን ዴቪልስ

7

ፎርትይ ስፖተድ ፓራዳሎትስ
(Forty-spotted pardalotes)

8

የአውስትራሊያ የእንጨት ዳክዬዎች

9

አጭር-መንቁራ እቺድናስ (Short-beaked echidnas)

10

ምስራቃዊ ባርድ ባንዲኩቶች (Eastern barred bandicoots)



## John Kamara (ጆን ካማራ)

John Kamara (ጆን ካማራ) ስደተኛ ሆኖ ወደ ታዝማኒያ መጣ። አሁን፣ እንደ ዘረኝነት፣ የጉልበት ብዝበዛ፣ እና የውጭ አገር የሙያ መመዘኛዎች እውቅና ማግኘትን የመሳሰሉ ስደተኞች የሚያጋጥሟቸውን የስርዓት ተግዳሮቶች ለማጉላት ይሰራል። John (ጆን) ስደተኞች ሥራ እና መኖሪያ ቤት እንዲፈልጉ ያግዛል፣ እና በመድብለ ባህላዊ መዘምራን ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋል። John (ጆን) የታዝማኒያ መድብለ ባህል ልዩነት ጥምረት መስራች እና ፕሬዝዳንት እንዲሁም የታዝማኒያ የአፍሪካ ማህበረሰቦች ምክር ቤት መስራች ነው። በ2023 የዓመቱ ምርጥ ታዝማኒያዊ አውስትራሊያዊ ነበር። John (ጆን) እና ባለቤቱ Mavis (ማቪስ) በሴራሊዮን እና በጋና ላሉ ተማሪዎች የትምህርት ግብአቶችን የሚያቀርብ የካማራ የልብ ፋውንዴሽን ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅትን አቋቋሙ። ለ John (ጆን) እና ቤተሰቡ፣ ታዝማኒያ አገራቸው ወይም ቤታቸው ነው፣ እና አላማውም ማህበረሰብ መፍጠር እና ለሁሉም የተሻለ፣ ፍትሃዊ ህይወት መፍጠር ነው።



## Mars Buttfield-Addison (ማርስ በተርፊልድ-አዲሰን)

Mars Buttfield-Addison (ማርስ በተርፊልድ-አዲሰን) የኮምፒውተር ሳይንቲስት እና የሳይንስ ኮሚዩኒኬተር ነች። በሕይወቷ እና በትምህርቷ ውስጥ አዲስ ጅምር ለመፈለግ በወጣትነቷ ወደ ታዝማኒያ መጣች። እንደ ቴክኖሎጂ ባለሙያ ማርስ በእይታ ንድፍ (visual design)፣ በሕዝብ ጤና፣ በኤሮስፔስ እና በሌሎችም ላይ ችግሮችን ፈትታለች። አሁን፣ በታዝማኒያ ዩኒቨርሲቲ፣ ሳተላይቶችን እና የጠፈር ፍርስራሾችን ለመከታተል የራዲዮ ቴሌስኮፖችን ታስተካክላለች። Mars (ማርስ) በሕዝብ እና በትምህርት ቤት የሳይንስ ቴክኖሎጂ እና ምህንድስና ዘርፍ (STEM) ፕሮግራሞች በኩል በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ደርሳለች፣ እናም በአውስትራሊያ ዙሪያ ባሉ ትምህርት ቤቶች እና የሳይንስ ዝግጅቶች ውስጥ ትምህርታዊ መተግበሪያዎችን እና ጨዋታዎችን አዘጋጅታለች። Mars (ማርስ) ታላቅ እድሎችን ለማግኘት ከታዝማኒያ መውጣት አለብህ የሚለውን ጊዜ ያለፈበትን ተረት ውድቅ ለማድረግ እና ትናንሽ ታዝማኒያውያንን እንኳን በዙሪያቸው ያለውን ሳይንስ እና ውበት እንዲያደንቁ ለማነሳሳት ትፈልጋለች።



## David Foster (ዴቪድ ፎስተር)

David Foster (ዴቪድ ፎስተር) ኦኤኤም፣ የዓለም ሻምፒዮን እንጨት ስንጣቂ (woodchopper) ሲሆን፣ ብዙ ጊዜ የአውስትራሊያ በጣም ስኬታማ አትሌት ይባላል። David (ዴቪድ) ያደገው በሰሜን ምዕራብ ታዝማኒያ ሲሆን ከአባቱ ጋር ባለ ሁለት እጅ እጥፍ የመጋዝ ቡድን ውስጥ የመጀመሪያውን የዓለም ዋንጫ አሸንፏል። በርካታ የአለም ክብረ ወሰኖችን በመስበር ለ21 ተከታታይ አመታት የአለም ዋንጫዎችን አስመዝግቧል። በአለም ላይ በየትኛውም የስፖርት አይነት በተለያዩ ደረጃዎች ከ1,000 በላይ ዋንጫዎችን በማንሳት ብቸኛው አትሌት ሊሆን ይችላል። David (ዴቪድ) በ2020 ወደ ስፖርት አውስትራሊያ የእውቅና መዝገብ ገብቷል፣ እና የታዝማኒያ የዓመቱ ምርጥ አውስትራሊያዊ እና የአንዛክ (ANZAC)፣ መቶኛ እና የአውስትራሊያ የክብር ሜዳሊያዎችን ጨምሮ ሽልማቶችን አግኝቷል። እሱ ለአረጋዊያን እንክብካቤ፣ ለወንዶች ጤና እና የተለያየ የጾታ ግንኙነት ማድረግ እምነት ላላቸው (LGBTQIA+) መብቶች ተሟጋች ነው። ለ David (ዴቪድ)፣ ታዝማኒያ በዓለም ላይ ለመኖር ምርጥ ቦታ ነች። እያንዳንዱ ወጣት ታዝማኒያውያን በራሳቸው የሚያምኑ ከሆነ ህልማቸው እውን ሊሆን እንደሚችል እንዲያውቁ ይፈልጋል።



## Carleeta Thomas ካርሊታ ቶማስ

Carleeta Thomas (ካርሊታ ቶማስ) የሰሜን ምስራቅ ሉትሩዊታ/ታዝማኒያ ኩሩ የፓካና ሴት ነች። Carleeta (ካርሊታ) የተወለደችው እና ያደገችው በትሩዊታ/ኬፕ ባረን ደሴት ሲሆን ከቤተሰቧ ጋር የማተን በርድ የሚባሉ ወፎች ለምግብ ማደን ትወዳለች። Carleeta (ካርሊታ) በዋካሊና (በማውንት ዊልያም ብሄራዊ ፓርክ) እና ላራፑና (ቤይ ኦፍ ፋየርስ) የሚሰራው የፓላዋ ንብረት የሆነ እና በፓላዋ የሚተዳደር የተሸላሚው የቱሪዝም ልምድ የዉካሊና የእግር ጉዞ መስራች አስጎብኚ ነበረች። Carleeta (ካርሊታ) “ወደ ዉካሊና ለመጀመሪያ የመጣሁበት ወቅት ወደ ትውልድ ሀገሬ የመጣሁበት የመጀመሪያ ጊዜ ነዉ” ትላለች። "ይህ የሰሜን ምስራቅ ብሔር ትሩውልዌይ ጎሳ የሚኖርበት ትክክለኛ ቦታ ነው። ወደ ማናላርገና (Mannalargenna) እንደገና ያገናኘናል። በቅድመ አያቶቼ ፊት በኬፕ ባረን ሃገር ስሆን የሚሰማኝ የግንኙነት ስሜት ተሰማኝ። በምጀምርበት ጊዜ ከቡድኖች ጋር የመነጋገር ልምድ አልነበረኝም። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያለሁ በራስ የመተማመን ነገር አልነበረኝም። በጊዜ ሂደት እራስህን ለመገንባት በአንተ አቅም የሚመለከቱ ሁለት ሰዎች ያስፈልጋሉ።

# ትንሸዋ ታዝማኒያዊት

# የካቲ የአትክልት ቦታ

አንድ እንዳንተ/እንዳንቺ የሚመስል ሰው አደረገው፣ እና አንተም/እንቺም ማድረግ ትችላለህ/ትችያለሽ!





ብራንድ ታዝማኒያ
ሆባርት፣ ታዝማኒያ፣ አውስትራሊያ | littletasmanian.com.au


የጽሑፍ እና ምሳሌዎች የቅጂ መብት © ብራንድ ታዝማኒያ 2024
መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።


የህትመት-ካታሎግ ዝርዝር ከአውስትራሊያ ብሔራዊ ቤተ-መጻሕፍት ይገኛል
ISBN 978-0-6459835-6-2


በShiloh Longbottom የተነደፈ እና የተገለፀ።


አብረው ያንብቡ + እዚህ ተጨማሪ

Forty South PUBLISHING

TASMANIAN


ISBN 9780645983562